# የአሰብ የአለኝታ ጥያቄ
# ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ አልሆነም ?

ከጌታቸው ጋረደው

ውይዘሮ አረጋሽ አዳነና አቶ ገብሩ አስራት አርያና ትግራይ ስለሚባለው አዲሱ ድርጅታቸው በታህሳስ መጨረሻ በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ቃለ ምልልስ አድርገው ነበር፣ የተናገሩት በክልላቸው ዴሞክራሲን ለማስከብር፣ የትግራይን ልኡላዊነት ለማስጠብቅ እንዲሁም የአሰብን ወደብ ለማስመለስ ያላቸውን አቅድ ለማስረዳት ነበር«

የወያኔ መሪዎችና ግብረ አአበሮቻቸው ስልጣን በያዙበት ወቅት ጀሌውም አህያ ነጂውም ሁሉም ተግበስብሶ ስለገባ፣ ስልጣን ለመያዝ ታማኝነቱ አንጂ ችሎታው ስላልተጠየቀ የመሀል አገር ህዝብ ሁሉም ታዛዥ ስለሆነ የወያነ መሪዎችና ተከታዮቻቸው ዛሪም አኛን የሚመለከቱን ምንም የማናውቅ ጅሎች አድርገው ስለሚያዩን ራሳቸውን እንደ አዋቂ አድርገው ስለሚመለከቱ የወይዘሮ አርጋሽና የአቶ ገብሩ አቀራርብ እንደ ወያኔ መሪዎች በመሆኑ አናዝናለን አነሱ ያሉትን አምነን ብንቀመጥ አነሱ እንደሚያስበት ጅሎች መሆናችንን ስለምናረጋግጥ አኛም የምናውቀውን በጥቂቱ እንነጋገር»፣ ከዚህ በታች የሰፈረው አስተያየት የትግራይን ህዝብ በፍጹም የማይመለከት መሆኑን በቅድሚያ አናሳስ ባለን.«

መለስ ዜናዊ በሻቢያ ድጋፍ በኦኤግ አጃቢነት በአሜሪካ መንግስት ጠባቂነት በ 1983 ለንደን ከተማ ተሰብስበው ኢትዮጵያን እንዴት እንደሚከፋፍሉ ተወያይተው ሲጨርሱ፣ የስብሰባው አደራዳሪ ሀርማንን ኸሀን ባቀረበው ሀሳብ፣ ኤሬትሪያ ከኢትዮጵያ ክተገነጠለች የአአሰብ ወደብ ለኢትዮጵያ መሆን ይገባዋል በማለት ሀሳብ ቢያቀርብ፣ መለስ ዜናዊ ጠረጴዛውን አየመታ፡ አሰብ የኤሬትሪያ ንብረት ነው በማለት ስለጮኸ ወይዘሮ አረጋሽና አቶ ገብሩ በስፍራው ባይገኙም የተሰበሰቡት ቡድኖች በብዛት ስለነበሩ የመለሰን ሀሳብ በጭብጨባ ተቀብለዋል፣ የኦኤግና የወያኔ መሪዎች አዲስ አእበባን በወረሩበት ውቅት የኢሳይያስ አፈወርቂን ትእዛዝ፡ ከመፈጸም ሌላ ያደረጉት ነገር የለም የአሰብ ጉዳይ አዚህ ላይ ተፈጸመ፣ የቀጠለው አጣዳፊ ስራ የመከላከያ ሰራዊትን መበታተን ስለነበረ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆነው ወታደር ያለ አንዳች የህይወት ዋስትና መሳሪያውን አያስረከበ ያለ በቂ ልብስ ያለ ጫማ በአግርና በመኪና ወደ አዲስ አበባ ተላከ፣ ሁኔታው የተማረክ |የውጭ ውራሪ ወታደር ይመስል ነበር፣ የቀጠለው አፋጣኝ ስራ የኤሬትሪያን መገንጠል ማፋጠን ስለነበር መለስ ዜናዊ የኤሬትሪያን መገንጠል ላተባበሩት መንግስታት ማሳወቅ ስለነበር፣ መለስ በጻፈው ደብዳቤ ኤሬትሪያ የኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት ስለሆነች ነጻነት እንድታገኝ በኢትዮጵያ መንግስት ስም አጠይቃለሁ ሲል ደብዳቤ ጻፈ፣ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈጸመው| የመጀመሪያው የክህደት ስራ ይህ ሲሆን መላ የውያኔ አባላት በህግም በታሪክም ተጠያቂዎች ናቸው»

መለስ ዜናዊ ይህንን አርምጃ በመውሰዱ ሁለት ስምምነቶችን አፈረሰ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤሬት ሪያንና ኢትዮጵያን በፈደራል አስተዳደር ሲያቀላቅል በስምምነቱ ሰነድ ላይ ያሰፈረው አንድ ማስጠንቀቂያ ቃል አንቀጽ 91 የሚለው፣ ይህንን የፌደራል ስምምነት በሙሉ ለማፍረስ ለመለውጥ ለመቀነስ ለመጨመር የሚችለው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ስብሰባ ብቻ ነው፣ ሁለተኛው ስምምነት ከቅኝ ግዛት ነጻ የወጡ አገሮች የጂኦግራፊ አቀማመጥ ትክክል ባይሆንም ሁሉም አገሮች የያዙትን ወሰን አክብረው እንዲኖሩ ይህንን ያላከበረ የመላ አፍሪቃ ጠላት ስለሆነ በጋራ አንቃወመዋለን ሲል ውሳኔ በማሳለፉ የግብጽ የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር የነበሩት ቡጥሮስ ቡጥሮስ ጋሊ ባሰሙት ንግግር ቤቱ የኢትዮጵያን ሀሳብ ስለደገፈ ኤሬትሪያና ሱማሊያ የኢትዮጵያ አካል ናቸው እንደሆኑም ይቀራሉ፣ የግብጽ መንግስት ይህንን ውሳኔ በሙሉ ይድግፋል በማለት ስለተናገሩ ቤቱ በሙሉ በከፍተኛ ጭብጨብ አመሰገናቸው፣ግን ኣኝህ አዛውንት ቃላችውን ባለማ ክነራቸውው በጣም አናዝናላን፣ ቡጥሮስ ቡጥሮስ ጋሊ ሀያ ስድስት አመታት ቆይተው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሀፊ ሆነው ስለተሾሙ የተናገሩትን ቃል ለውጠው ኤሬትሪያ የኢትዮጵያ

<የቅኝ ቅኝግዛት ስለሆነች ነጽነት ማግኘት ይገባታል በማለት ከመለስ ጋር ለመነጋገር ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አንድ ተማሪ በፖሊስ ተገሎ ሞተ፥ ቡጥሮስ ቡጥሮስ ጋሊ ቃላቸውን በመለወጥ ብቻ ሳይወሰኑ የአአፍሪቃን አንድነት ድርጅት ይሳለፋትን ውሳኔ ለውጠው በተጭበረበረ መንገድ ተጠቀሙበት፣አንደኛ ድርጅቱ በአንቀጽ 91 እንዳስጠነቀው የፌደራሉን ስምምነት ለማፍረስ ጠቅላላ ስብሰባ አልተደረገም፣ ሁላተኛ የኤሬትሪያ ህዝብ ረፈራንዱም እንዲያደርግ አእንድም የድርጅቱ ባለስልጣን አልወሰነም፣ ይህንን በማድረግ ፈንታ ቡጥሮስ ቡጥሮስ ጋሊ ከአሜሪካ መንግስትጋር በማሴር ውሳኔውን በምስጢር ብድብቅ ለጸጥታው ምክር ቤት አቅርበው ሲያስወስኑ በመጨ ረሻ ሁሉም ነገር ትክክለኛውን መንገድ ይዞ እንደተሰራ በማስመሰል ሬፈራንዱም ኣንዲደረግ ሲታዝዝ ምርጫህ ባርነት ውይም ነጽነት ነው ሲባል ኤረትራውያን ነጻነትን መርጠው ባሮች ሆነው ቀሩ፣ በነጻነት ኣወጃው እለት መለስ ዜናዊ እንደ ቅኝ አገር ገዥ አስመራ ተገኝቶ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አአላማ ወርዶ የኤሬትሪያ ሲሰቀል የአይን ምስክር ለመሆን ቻለ፣ ባለፋት ሶስት ሺህ አመት ታሪካችን በብዙ መቶ የሚቆጠሩ መልካምና መጥፎ መሪዎች ቢያጋጥሙንም እንደ መለስ ዜናዊ ያለ ክፉ አረመኔ ክሀዲ መሪ አጋጥሞን አያውቅም፣ ውይዘሮ አረጋሽና አቶ ገብሩ በነጻነት አወጃው እለት በአካል አስመራ ባትገኙም ለአእስራ ሰባት አመታት ያደረጋችሁትን የትግል ውጤት ለማየት በመቻላችሁ የሚቀጥ ለውንም ለማየት ለሁላችንም እድሜ ይስጠን፣ እኛም የእናንተ ሰለባ በመሆን ያደማችሁትን ልባችንን ይዘን እስከ ዝንተ አለም እንረሳችሁም፥

ኢሳይያስ አፈወርቂ ካኢትዮጵያ ወታደሮች የማረከውን የጦር መሳሪያ ዘመናዊ የሆኑትን በሙሉ ወደ አስመራ ወስዶ የበለጠውን ለላቲን አሜሪካ አገሮች ሽጦ ገንዘቡን ለራሱ ሲየስቀር መለስ ለመከላከል አልቻለም፣ በዚህ አይነት አገሪቱን ያለ ወታደር ያለ መሳሪያ ሲያስቀር፣ ኢሳይያስ ወሰኑ ያለ ጠባቂ እንደቀረ ስለተመለከተ አንድ ጥይት ሳይቶኩስ አካባዊንና ባድምን በቁጥጥሩ ስር አዋለ፣ የውያኔ ጀሌ ወታደሮች የሻቢያን ሀይል ለማቆም ስለአልቻሉ መለስ ወረራውን ተቀብሎ ድምጹን አጥፎቶ ተቀምጠ፣ የመከላከያ ሰራዊቱ ስለተበታተነ በአጭር ጊዜ ለማሰባሰብ አልተቻለም መለስ ዜናዊ ለኢሳይያስ ያለውን ፍቅርና ታማኝነት ለማሳየት የሰራው ምህረት የማይገባው ስህተት አገሪቱንና ህዝቡን ለክፍተኛ አደጋ ላይ ጣለ፣ በየስፍራው የተበታተነውን ወታደር አሰባስቦ ለማዝ መት ከስድስት ወራት በላይ ሲፈጅ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ትብብር ስለአደረገ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወታደሮቻችን የተያዘውን አገር ነጻ ከማድረግ አልፈው የአሰብን ወደብ ለመያዝ ሰላሳ ሰባት ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው፣ መለስ ከአንቅልፋ ነቅቶ ወታደሩ አሰብን እንዳይዝ እንዲያፈገፍግ ስለአዘዘ፣ ወታደሩ መመለስ ሲገደድ የሻቢያ ወታደሮች ክጀርባ መጥተው በብዙ መቶ ሚቆጠሩ ወታደሮቻችን ትርጉም ለሌለው ጦርነት በከንቱ ህይወታቸውን ሰጡ፣ ጦርነቱ እንደተፈጸመ የወያኔ ጀሌ ወታደሮች ወሮ ወሸባዬ እየተዘፈነላቸው በክበሮና በእልልታ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የኢትዮጵያ ወታደሮች መሳሪያቸውን አስረክበው በእግር ጉዞ ወደ ክልላቸይህ ሲሄዱ ይህ ሳይበቃቸው ጀብዱ የፈጸሙ ወታደሮች ተመርጠው ሽልማት እንዲያገኙ ስለተደረገ፣. ክሶስት ሚሊዮን የትግራይ ህዝብ ሰላሳ ሰባት ጀግኖች ሲሸለሙ፣ ከሰባ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ሶስት ጀግኖች፣ብቻ ተሸልሙ ይህ አያሳዝንም፣ ወታደሩን ጦር ሜዳ ልኮ እንዳይዋጋ ከልክሎ ጠላት ከጀርባው ተኩሶ እንዲገለው ካደረገ ይህ የአገር መሪ መለስ ዜናዊ ጦር ፍርድ ቤት ቅርቦ መቀጣት ሲገባው አሁንም ስልጣን ይዞ ህዝብ ስቃያል፣ ይህ ግፍ ይህ በደል አያስጠይቅም ሀሊናን አይነካም፣ ወይዘሮ አረጋሽና አቶ ገብሩ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ስለተመለከታችሁ ምን ትላላችሁ?

መለስ ኤሬትሪያ በባድማ ጦርነት ስለተሸነፈች በጣም በማዘኑ ይህንንም ውርደት ተቀብሎ ማለፍ ስላአእቻለ በሁለቱ እአገሮች መካከል ያለው የወሰን ጉዳይ በሽማግሌዎች እንዲታይ መለስ ሀሳብ ስለ አቀረበ ላኡካን ወደ አልጀሪያ ሄዱ፣ የስብሰባው ተካፋዮች ብዙውቹ ቢሆኑም ኢትዮጵያውያን መስልው የገቡ ኤሬትራውያን ነበሩ፣ ስብሰባው እንደተጀመረ ጉዳዩ ሆላንድ በሚገኘው አእለም ፍርድ ቤት እንዲታይ ሲወሰን መለስ ዜናዊ ሳይጠየቅ ሳየይገደድ፣ ፍርድ ቤቱ የሚስጠውን ማናችውንም ውሳኔ ያለ ይግባኝ በመቀበል በተግባር እውሳለሁ በማለት ቃሉን ሰለሰጠ ኤሬትራውያን እንዲሁም እትዮጵያውያን ነን ባዮችም ችግራቸው ተወገደላቸው፥ ከሳሽም ተከሳሽም ፍርድ ቤት ክርክራቸውን ቀጠሉ፣ የመለስ ፍላጎት ኤሬትራውያን እንዲያሸንፉ ስለሚፈልግ አገር በቀል ጠበቆች አውነተኛውን ሀቁን ስለሚናግሩ እነሱን አግልሎ ጣሊያኖችን ስለቀጠረ የጣልያን ጠበቆች የተጠየቁትን ማናቸውንም ጥያቄ ባላጋራን በሚጠቅም አዎንታዊ መልስ ከመስጠት ሌላ ያሰሙት ነገር የለም፣ በኤሬትሪያ በኩል

የቀረበው ማስረጃ በአውሮፓ አአቆጣጠር በ 1901 02 እና 08 የጣሊያን መንግስት ያዘጋቸው ሲሆኑ፣ የኢትዮጵያ ንጉስ ክጣሊያን መንግስትጋር ተፈራርመዋል ቢባልም ንጉስ ነገስቱ እጼ ምንሊክ ወይም ወኪላቸው የፈረመበት ሰነድ አእልተገኝም ዳኞች አልጠየቁም፣ የመለስ ጠበቃም ድምጹን አላሰማም፣ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው መጨረሻ ባድሜን ለኤሬትራ የፈረደው የሚያደርገው ስለጨነቀው ከችግር የተነሳ ነው፣ ምክንያቱም የኤትሪያው ጠበቃ ለሚያቀርበው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ አያገኝም ወይም አንድ የሳር ግጦሽ ቦታ የኢትዮጵያ ነውን ብሎ ዳኛው ሲጠይቅ የመለስ ጠባቃ ምንም መልስ አይሰጥም ወይም የኢትዮጵያ አይደለም ይሚል መልስ ይሰጣል፣ ከላይ እንደተጠቀሰው መለስ የኤሬትሪን መሸነፍ ለመቀበል ስለአእልፈገ በዚህ አይነት ዝዴ መጠቀም ተገደደ፥ ፍርድ በተሰጠበት ቀን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስዩም መስፍን በስፍራው ተገኝቶ ስለነበር ወድ ውጭ ሲወጣ፡ በጣም ተደና ግጦ ስለነበር በፈጥነት መኪና ውስጥ ገብቶ ፈረጠጠ አዲስ አበባ ሲገባ የምስራች ደስ ይበላችሁ ደስ ብሎናል በጦርነት ያሸነፍነውን በፍርድም ደገምነው ከፈለግነው በላይ ተፈረደልን ብሎ በውሸት ህዝቡን ስለ አስደሰተ የትግራ<ይ ህዝብ ሶስት ቀናት ሙሉ ከበሮ እየመታ እንቢልታ እየነፋ ሲጨፍር ከረመ<፣ በመጨረሻ የኤሬትሪያ ራዲዮ ውሸት መሆኑን ስለገለጸ ህዝቡ የተደሰተውን ያህል በዚያው ልክ ሲያለቅስ ከረመ፣ በመጨረሻም መለስ ውሳኔውን አሻፈረኝ ስላለ ወሰኑ በችካል ሳይሆን በካርታ ተሰሎ እንዲሰጣቸው ፍርድ ቤቱ ሲወስን፣ ኢሳይያስ ሲቀበል መለስ እምቢ አለ፣ የኢሳይያስ ውሳኔ ብል ህነት ነው ምክንያቱም ወረቀት ቂል ስለሆነ ዛሬ የጨሩበትን ለመቶ አመት ይዞ ቁልጭ አድርጎ. ስለሚያሳይ የኢሳይያስ የልጅ ልጆች አንድ ቀን ይህንን ወረቀት ለልጆቻችን አቅርበው ባድሜን ያገኙ ይሆናል፣ መርሳት ማይገባን አንድ ነገር አላ፣ መለስ ዜናዊ ባድሜን ለኤሬትሪያ አሳልፎ የሰጠው ሳያንሰው ከጎንደር ግዛት እንደአባቱ ጉልማ እየቆረጠ ለሱዳን ይሰጣል፣ በለውጡ የሱዳን መንግስት ሱዳን የሚገኙትን ኢትዮጵያውያን ስደተኞች እያሰረ ለመለስ ያስርክባል፣ ወይዘሮ አረጋሽና አቶ ገብሩ ስለዚህ የሰው ህይወት በመሬት የመለወጥ ንግድ ምን ይላሉ፣ የጎንደርንና የወሎን መሬት በመሳሪያ ሀይል ነጥቀው ሲወስዱ ሱዳን የሚገኘውን መሬት በወንድሞቻቸው ህይወት ለውጠው ሲቀመጡ ህሊናችው አይወቅሳችውም፣ የማይገኘውን አስብን እናስመልሳለን በማለት ጊዚያቸውን በከንቱ ክማባከን መለስ በኢትዮጵያ መሬት ኢትዮጵያውያንን እየገዛ እንዳይገላቸው ቢያደርጉ መላ ያኢትዮጵያ ህዝብ ባለውለታችው በሆነ ነበ.«

ወይዝሮ አረጋሽና አቶ ገብሩ በትግራይ ዴሞክራሲ እንዲክብር የአገሪቱ ሉኡላዊነት እንዲጠብቅ ጥረት አናደርጋለን ይላሉ፣ አየገሪቱ አንድነትና ስለ መገንጠል አንቀጽ 39 ምን ታስባላችሁ ለሚለው ጥያቄ ሲመልሱ፣ ኦሮሞና ኡጋዴን ለመገንጠል ስልሚፈልጉ ልንከለክላችው አንችልም ላእኛም እንዲሁ አናስባለን ብለዋል፣ የእነሱ ድርጅት አዲስ ቢመስልም እንደሰማነው እንደ ወያኔ ድርጅት የጎሳና የዘረኞች ድርጅት ከመሆን አልፎ የወያነ ወራሽ ተረካቢ ድርጅት ነው ይባላል፣የአርያና ድርጅት መሪዎች ትግል ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ለመገንጠል ፈላጊዎች ናቸው፣ ኢትዮጵያ ዛሬ የደረሰችበት ደረጃ ለመድረስ አባቶቻችን ብዙ ደክመዋል.፣ መልካም ጨዋ ህዝብ፣ የሚያኮራ ታሪክ ያለው፣ታታሪ አንግዳ ወዳድ፣ ተፈጥሮ ያበለጸገው ህዝብን በታትኖ ማንን ለማምጣት ነው ገንጠላው የተፈለገው ታሪካችንን መለስ ብለን ብንመለከት በአድዋ ጦርነት ሆነ በአእምስቱ አመት የጣሊያን ውረራ ጠላት የደፈረን የትግራይን_ግዛት መሸሸጋገሪያ አእድርጎ ስለነበር፣ የትግራይ አባቶች ክንዳችንን ሳንንተራስ ጠላት የኢትዮጵያን መሬት አይረግጣትም በማለት ደማቸውን አእፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ያስረከቡንን አገር፣ የእነሱ የልጅ ልጆች መለስ ዜናዊና የባእድ መንግስት ተቀጣሪዎች፣ በጀግኖች አባቶቻቸው አጽም ላይ እየተረማመዱ ኢትዮጵያን በታትነው ለመሄድ ስለ ተዘጋጁ እኛም ክንዳችንን ሳንተራስ እናት አትዮጵያ አትበታትንም፣ይህንንም ቃላችንን በተግባር ለማዋል የኢትዮጵያ አምላክ አይለየን

ወይዘሮ አረጋሽና አቶ ገብሩ ስለ ትግራይ ክልል ልኡላዊነት ይናገራሉ፣ ይህ ልኡላዊነት ምን ያህል ትልቅ ነው፣ ክአባቶቻችሁ የወረሳችሁትን ብቻ ወይስ በ 1983 ኢትዮጳያን በወረራችሁብት ወቅት ክጎንድርና ከወሎ ክልል የእገሬውን ህዝብ አባራችሁ በመሳሪ<ያ ሀይል የዘረፋችሁትን በእንድነት ደባልቃችሁ፣ይትግራይ ክልል ነው ትላላችሁ፣ እናንት ከላይ በተጠቀሰው አመተ ምህረት በብዙ ሺህ የሚቆጠር የወያኔ ወታደሮች አምጥታችሁ የጎንደርንና የውሎን ህዝብ በሙሉ አፍሳችሁ ከአገሩ እንዲባረር ስላደረጋችሁ ክጎንደር ሴቲቱ ሁመራ፣ ወልቃይት ጠግዴን እንዲሁም ከወሎ የአላምጣ የኮርም ህዝብ ከተወለደብት ካደገበት መንደር በራሱ አገር ኩሊኒት ሰርቶ እንዳይኖር ስለተባረረ

አገሩን ለቆ መሰደድ ተገደደ ይህ አግባብ ነው፣ የጎንደርና የውሎ ህዝብ ውታደሩን አስስታጥቆ የትግራይን ክልል በመውረር የመቀሌን የእድዋን ህዝብ በመሳሪያ አስገድዶ ቢያባርረው የአርሽ መሬቱን ቢነጥቀው አልፎ ተርፍ አገሩን ለቆ እንዲሰደድ ቢያስገድደው፣ የእናንተ ስሜት እንዴት ነው፣ ኢትዮጵያን ለባአድ ምንግስት ሽጣችሁ በለውጡ ባገኛችሁት የጦር መሳሪያ ወግታችሁ ታባርራላችሁ ወይስ እንደ ጎንድርና እንደ ውሎ ህዝብ እጃችሁን አጣምራችሁ ትመለከታላችሁ፣ ሰው የወንድሙን አገር አይወርም፣ይህ ትክክል እንዳልሆነ ከተሰማችሁ የያዛችሁትን የሰው መሬት ለባለ መሬቱ አስረክባችሁ ውደ መጣችሁበት የምትመለሱበት ጊዜ አሁን ነው፣ የዛሬ ደካማ ነገ ሊጠነክር ይችላልና፥

አረሱት የወልቃይትን መሬት ያውም የኛን እጣ

እነሱ ምን ያርጉ ክኛ ሰው ክታጣ

ንዳቸው ላሞቹን አቧራው ይነሳ

ይከተላቸዋል ኮርማው አያገሳ

ይህንን ጽሁፍ ክመደምደማችን በፊት ስላራሳችን ጉዳይ ብጥቂቱ እንነጋገር፣ መለስ ዜናዊና የወያኔ ወራሪዎች ኢትዮጵያን ከወረሩ አስራ ሰባት አእመታት አለፉ፣ እኛም በተቃዋሚነት ተመሳሳይ ጊዜ አሳልፈናል፣ ወያኔዎች በዚህ ጊዜ እነሱን የሚጠቅም ብዙ ነገር ሰርተዋል አገሪቱን የሚጎዳ ብዙነገር አበላሽተዋል፣ እኛስ ምን አለማን ምን አበላሸን፣ ይህንን ጥያቄ የምናቀርበው ማንንም ልመውቀስ ወይም ለማወደስ አይደለም ሁላችንም የሰራነውን መልካምና መጥፎ ነገር ስለምናስታውስ መልካሙን ስራችንን ለመደጋገም መጥፎውን ለማረም እንዲረዳን ህሊናችን ይፍረድልን ወይም ይፍረድብን በቅንጅት መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ብዙ ተወቃቅሰናል ተሰዳድበናል ያልተግባባነው በግል ጉዳይ ሳይሆን በፖለቲካ ምክንያት ነው ማናችውም ሰው የራስ አእስተሳሰብ አለው፣ አንዱ የተናገረውን ሌላው መስሎ ካልታየው መቀበል የለበትም አክሩፎ ወዲያው መሄድ የለበትም፣ የመጀመሪያው ተናጋሪ ጥቂት አረፍት አድርጎ መነሻውን ሳይረሳ ሌሎች ቃላት ጨማምሮ እንድገና ለመወያይት ቢሞክር ለመግባባት ይችል ይሆናል፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ያፖለቲካ ውይይት ለማድረግ ትእግስት የለንም፣ መቻቻል መደማመጥ አንችልም፣ ሆደ ባሾች በመሆን ፖለቲካውን እንድ ግል ጉዳይ ወስደን ከደህና ባልንጀራችን ጋር እንቀያየማለን እናኮርፋለን፣ ሰለጠኑ የሚባሉ አግሮች በፖሊቲካ ጉዳይ ተሰብስበው ሲወያዩ በጣም ያስቀናሉ፥ እኛ መደገም የማይገባው ብዙ ስህተት ሰርተናል፥ የተጎዳነው እኛና አገር ቤት ያለው ህዝባችን ስንሆን ተጠቃሚው መለስና ወያኔዎች ብቻ ናቸው፣ ክ 1997 በፊት ገበሬው ማዳበሪያ ለመግዝያት በአጥፍ ይከፍል ነበር፣ ዛሬ በነጻ ይሰጠዋል፣ ወጣቶች ቀኑን ሙሉ በነጻ ለሰላሳ መጠጥ እየጠጡ ሲዝናኑ ይውላሉ፣ መለስ በዚህ አይነት ዘዴ ገበረውንና ወጣቱን የሚያሽኮረምመው በሚመጣው ምርጫ ለማሸነፍ በማሰብ ነው፣ ብ 97 ምርጫ የገበሬውን ድምጽ ለማግኘት ገበሬውን በጥቅም ለመግዛት ሞክሮ አልተሳካለትም፣ የሚቀጥለው ምርጫ እንዴት ይሆን፣ ከሶስት ወራት በላይ እርስ ባርሳችን ስንነካክስ ጊዜውን ሰላባከንን ዋጋውን እንክፍል ይሆናል፣ ካስህተታችን ከተማርን ህዝባችን ይቅርታ ካደረገልን ግባችን እንደርስ ይሆናል፡፡ የቅንጅት መሪዎች በህብረት ከሰሩ አሰዬ ደስ ይለናል፣ በህብረት ቢሰሩም ባይሰሩም እንድ ተጨማሪ እቅድ እየተዘጋጀ ነው፣ ክ 1983 ጀምሮ አገራችን በአእንድ ሰው ፈላጭና ቀራጭ መሪ ስር ስለሆነች በፖላቲካ፣ በኤኮኖሚ ወይም፣በማህበራዊ ኑሮ በፍጹም ተካፋይነት ሰለሌለን በራሳችን አገር ባእድ፣ የበላተኛ ተመልካች ሰባእዊ መብታችን ያልተከበረ በሁለተኛ ደረጃ ዜግነት የምንኖር ስለሆንን ክሰላማዊ ትግል ተጨማሪ የአርበኞች ንቅናቄ ቢታከልበት የትግሉን አድሜ ሊያሳጥርልን የሚችል ከመሆኑ ሌላ መለስ ዜናዊ የሰላሙን ትግል እንዲቀበል ይገደድ ይሆናል፥

በ 1928 የጣሊያ ፋሽሽት አገራችንን በውረረበት ጊዜ የአገሪቱ መሪ የነበሩት ንጉስ ሀይለ ስላሴ ህዝቡን ላጠላት አጋፍጠው ወደ እንግሊዝ አገር በኮበለሉበት ወቅት ዘማቹ ህዝብ ያለ መሪ ስልቀረ ጊዜ የወለዳቸው ጀግኖች እነ በላይ ዘለቀ፣ ገረሱ ዱኪ አበበ አረጋይና ሌሎች አርበኞች ተዋጊውን አሰባሰበው በየጦር ሜዳው ስለላኩት፣ አርበኛው ለአምስት አመታት ጠላትን መግቢያና መውጫ በማሳጣት ለነጻነት አበቁን፣ እነዚህ ጀግኖች ግዳጃቸውን ፈጽምው ለዝንተ አእለም ቢያሸልቡም ያነሱ ልጆች የአባቶቻቸውን ጋሻ ተሸክመው ዱር ቤቴ በማለት አባቶቻቸው ወደነበሩበት በረሀ ለመሄድ ተዘጋጅተዋል፣ መለስ ዜናዊ የሰላሙን ጥሪ ካልተቀበለ በሚገባው ቃላት ማነጋገር አስፈላጊና ጊዜውም ዛሬ ነው፣ በዚህ ንቅናቄ መሪና ተመሪ የለም፣ ለአቅመ አዳም የደረስህ ጎልማሳ አምዬ ኢትዮጵያ ትጠራሀለች ድምጽህን አሰማት«አምላክ ከአንተ ጋር ይሁን፥

ፍራንክፈርት ጥር 11/2000 20. 01.2008